<u>የቴዲ አፍሮ አድናቂዎች እና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በለንደን የቁም ሰልፍ አካሄዱ</u>

ትላንት ሜይ 06፡ 2008 ዓ. ም. (እ.ኤ.አ) በለንደን የሚገኙ የቴዲ አፍሮ አድናቂዎች እና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በአርቲስቱ ላይ የተፈፀመውን የብቀላ እስር በመቃወም በኢትዮጵያ ኤምባሲ ፊት ለፊት የቁም ሰልፍ አድርገዋል። ከቀኑ 10.00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 1.30 ሰዓት ድረስ በተካሄደው በዚሁ የቁም ሰልፍ ላይ ከተያዙትም መፈክሮች ውስጥ፡

ቴዲ አፍሮ ይፈታ!
ቴዲ አፍሮ ወንጀለኛ አይደለም!
በኢትዮጵያ ያሉ ሁሉም የህሊና እስረኞች ይፈቱ!
በግፍ የታሰሩ ሁሉም ጋዜጠኞች ይፈቱ!
ዘረኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ያብቃ!
ፍትህ፡ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ!
እኩልነት ለሁሉም!

የሚሉት ይገኙበታል። ከመፈክሮቹ በተጨማሪም “ያስተሰርያል” የሚለውና ሌሎችም የህሊና እስረኛው ድንቅ ዜማዎች በሰልፉ ተሳታፊዎች ኅልተው ይዘፈኑ ነበር። የሰልፈኞቹ ተጠሪዎች በፖሊስ ታጅበው ያዘጋጁትን የተቃውሞ ደብዳቤም ለኤምባሲው አስገብተዋል። ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል፡ ሌሎችም የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችና የዲፕሎማቲክ ቢሮዎች ሁኔታውን የሚያሳውቅ ደብዳቤ በየአድራሻቸው ልከዋል። በተጨማሪም የፈጠራ ክስ ተመስርቶበት ወደእስር ቤት የተወረወረው ቴዲ አፍሮ በነፃ እስኪለቀቅ የተቃውሞ ድምፃቸውን እንደማያቆሙ አሳውቀዋል።